# በቅንጅት ስም የተሰበሰበው ገንዘብ የማነው?

## *ድጋፍ አሰባሳቢዎቹ መልስ አላቸው*

ቅንጅት ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ አመራር አባላት ክፍፍል መስመር እየያዘ ነው። ከእስር ቤት የተፈቱት አመራር አባላት በሦስት ተከፋፍለዋል። አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ፣ ግንቦት 7 ንቅናቄ እና በቅንጅት ስም ክስ አቅርበው በመኢአድ ስም ስብሰባ የጠሩት በኢ/ር ኃይሉ ሻውል የሚመራው ቡድን ናቸው።

በኢ/ር ኃይሉ ሻውል የሚመራው ቡድን ቅዳሜ ሰኔ 13 ቀን እና እሁድ ሰኔ 14 ቀን 2000 ዓ.ም. ጠቅላላ ጉባዔ አድርጓል። የጠቅላላ ጉባዔው ጥሪ ለአባላቱም ሆነ ለተጋባዡ እንግዶች የተላለፈው በቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ስም ሲሆን፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስብሰባ ማሳወቂያ ክፍል በመኢአድ ስም እንዲደረግ ብቻ በመፍቀዱ ጉባዔው በመኢአድ ስም ተከናውኗል። ነገር ግን ስብሰባው የተመራውም ሆነ ምርጫ ተደረገው፣ መግለጫ የተሰጠው በቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ስም ነበር።

በጠቅላላው ጉባዔ ም/ፕሬዝዳንትና የሰሜን ኢትዮጵያ ቀጠና ኃላፊ ሆነው የተመረጡት አቶ አባይነህ ብርሃኑ፤ በእሁዱ የጠቅላላ ጉባዔ መዝጊያ ላይ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተው ነበር። አመራሮቹ ከእስር ከመፈታታቸውም ሆነ ከተፈቱ በኋላ በውጭ አገር የሚገኙ ቻፕተሮች ገንዘብ በማሰባሰብ ለፓርቲው የሚሰጡት እርዳታ ከፍተኛ ሲሆን፣ ቻፕተሮቹ ያሰባሰቡት ገንዘብ በቅንጅት ስም በመሆኑ ሊመልሱላቸው እንደሚገባ አቶ አባይነህ አምርረው ተናግረዋል። ይህ ካልሆነ ግን ጉዳዩን ወደ ሕግ በመውሰድ ገንዘቡን ገቢ እንደሚያደርጉም ዝተዋል።

ገንዘብ በማሰባሰብ የሚታወቁት በአሜሪካ በተለያዩ ስቴቶች የሚገኙ ቻፕተሮች ሲሆን ዋሽንግተን ዲሲ፣ ቦስተን፣ አትላንታ፣ ጌነስ፣ ኒውዮርክ ሲቲ፣ ዳላስ፣ ዴንቨር፣ ላስ ቬጋስ፣ ሲያትል፣ ሚኔሶታ፣ ኦሃዩ፣ ሎስ አንጀለስ፣ ሳን አዜ እና ደቡብ ዳኮታ የሚገኙት ናቸው።

አቶ አክሎግ ልመንህ ይባላሉ በአሜሪካን ቦስተን ነዋሪ ሲሆኑ፣ የቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ አሰባሳቢ ማኅበር ሊቀመንበር ናቸው። ***ቅንጅት በሚል ስም ሲሰበሰብ የነበረው የነበረውን ገንዘብ እንዴት ታረጉታለችሁ ባለቤቱስ ማነው?*** በሚል ጥያቄ አቀረብንላቸው።

አቶ አክሎግ ጉዳዩን ሲያብራሩ፤ ድርጅቱ መኢአድ ብቻውን በነበረ ጊዜ ለሱ ድጋፍ በማሰባሰብ ተቋቁሞ እንደነበረ ገልጸው፤ ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ሲቋቋም ግን ወደ ቅንጅቱ መቀላቀሉን ገልፀዋል።

ከሁለት ዓመት በፊት መሪዎቹ እስር ቤት በነበሩበት ወቅት በተፈጠረ አለመግባባት ማኅበሩን በሊቀመንበርነት ከሚያስተዳድሩት ሻለቃ ዮሴፍ እና ከተወሰኑ የአቶ ኃይሉ ደጋፊዎች ጋር አለመግባባት መፈጠሩንና አቶ አንዳርጋቸው ፅጌንና አቶ ብርሃነ መዋን በማገዳቸው ጉዳዩን የተቃወሙ በሙሉ አትላንታ በመሄድ ስብሰባ ያደርጋሉ።

በአቶ ኃይሉ የተደራጀው ያኛው ቡድንም ዴንቨር ሄዶ ስብሰባ ማድረጉን ገልፀው በወቅቱ ሰብስቦ በቅንጅት ካዝና ውስጥ የነበረውን ከ230 ሺህ ዶላር በላይ ይዘው መገንጠላቸውን ገልፀው "እኛ አትላንታ ስብሰባ ካደረግን በኋላ ከአሜሪካ መንግሥት ታክስ ነፃ ተደርገን እንደ ግብረ ሰናይ ድርጅት የሚቆጠር ማኅበር ነው ያቋቋምነው። ማኅበሩ ሲቋቋም የእነ አቶ ኃይሉን ወይም ዶ/ር ብርሃኑን አሊያም ወ/ት ብርቱኳንን ቡድን እንደግፋለን በሚል ግለሰቦችን ለመርዳት ሳይሆን በመተዳደሪያ ደንባችን ላይ በግልፅ እንደተቀመጠው በኢትዮጵያ በሠላማዊ ትግል ተንቀሳቅሰው ዲሞክራሲን ለማምጣት ትግል የጀመረውን የቅንጅት ኃይል ለመደገፍ የተቋቋመ ማኅበር ነው።" ብለዋል።

አያይዘውም ቅንጅት የተነሳለትን ዓላማ ይዞ በሠላማዊ ትግል የመቀጠልና የማስፈፀም ብቃት አለው ብለው የሚያምኑት ደግሞ በአዲሷ ሴት ሊቀመንበር የሚመራውን አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ እንደሆነ ተናግረዋል።

***በእነ አቶ ኃይሉ ሻውል በሕግ ልትጠየቁ አትችሉም?*** ወይ በሚል ላቀረብንላቸው ጥያቄ "ድርጅታችን" 18 ቻፕተሮች ያሉት ማኀበር ነው። ቻፕተሮቹ ደግሞ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ አባላት አሏቸው። የኛ ድርጅት ደግሞ እነዚህን ቅርንጫፎች በማዕከልነት ያሰባሰበ ነው።

ስለዚህ እኛን ገንዘብ የሚጠይቁን እነ አቶ ኃይሉ አይደሉም፤ የተቋቋምነውም ለግለሰብ ለመስጠት ሳይሆን የቅንጅት ወራሽ ለሆነው አንድነት ፓርቲ ነው። ድርጅታችን ደግሞ በአሜሪካን ሕግ መሰረት የተቋቋመ ሲሆን፣ አንድም የምንጠየቅበት የሕግ አግባብ የለም ብለውናል።

ይልቅ በክፍፍሉም ወቅት ሆነ ከክፍፍሉ በኋላ ይዘው የሄዱት ወገኖች የሳቸው ሆነው ሳለና እኛም ከሁሉም በላይ አገሪቱ አጣብቂኝ ውሰጥ ባለችበት ሁኔታ ወደ መካሰስ መሄዱ ለማንም አይጠቅምም በሚል መተዋቸውን ገልፀው "የሚያሳዝነው ተቃዋሚ ፓርቲዎች የግል ወይም የፓርቲ ቡድናቸውን ወደ ኋላ ትተው ትልቁን የሀገር ህልውና በማስቀደም ለህዝቡ ምላሽ በሚሰጡበት ሁኔታ መዋቀር አለባቸው" ብለዋል። "እነ አቶ ኃይሉ ፓርቲውን አጠናክረው ወደፊት መሄድና መሥራት ሲገባቸው ገና ጠቅላላ ጉባዔ ከማካሄዳቸው "ወደ ክስ እንሄዳለን" የሚል መፈክር ማሰማታቸው አሁንም ከሽኩቻ በፀዳ መንፈስ ለትግል አለመነሳታቸውን ያሳያል" ሲሉ አቶ አክሎግ አብራርተዋል።

***የድጋፍ አሰባሳቢ ኮሚቴው ከዶ/ር ብርሃኑ ጋር ያለውሰ ትስስርስ?*** በሚል ለጠየቅናቸው ጥያቄ፤ "ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ከአንድነቱ መለየታቸውን በግልፅ ያስቀመጡ የራሳቸውን ምርጫ የወሰኑ ሰው ናቸው። ይህን መብታቸውን እናከብርላቸዋለን። ገንዘቡ ሲሰባሰብ ግን ለዶ/ር ብርሃኑ ወይም ለወ/ት ብርቱካን ሳይሆን የቅንጅትን መርሆዎች በሕጋዊ መንገድ ተከትሎ ተግባራዊ ለሚያደርግልን አካል በመርዳት የኢትዮጵያን ህዝብ የሥልጣን ባለቤት ለማድረግ ነው። በአሁኑ ሰዓት ደግሞ ሕግና ደንቡን አክብሮ የሚሠራ አንድነት ፓርቲ ነው። እሱን ነው የምንደግፈው።" በማለት አቶ አክሎግ መልስ ሰጥተውናል።

***በቫንኮቨር፣ ቶሮንቶ፣ ካልጋሪ፣ ዋተርሉና ዊኒፔግ*** የተባሉ አምስት ቻፕተሮች በካናዳ ይገኛሉ። የዚህን አስተባባሪ አቶ የሱፍ ዑመርን ስለጉዳዩ አነጋገርናቸው፤ ቀደም ሲል በካናዳ በመኢአድ ስም የሚንቀሳቀሱ እንደነበሩ ገልፀው የቅንጅት አመራሮች ለእስር በተዳረጉበት ወቅት በጋራ ሆነው ሲንቀሳቀሱ እንደነበር አስረድተዋል። በመጨረሻ በመካከላቸው መግባባት ሊፈጠር ባለመቻሉ አዲስ ምርጫ እንዲደረግ ሲጠይቁ ፍቃደኛ የሚሆን አካል በመጥፋቱ ራሳቸውን አግልለው ለብቻቸው በመሥራት ላይ እንደሚገኙ ገልፀዋል።

"ነገር ግን በወቅቱ የነበሩ የተወሰኑ የቦርድ አባላት የአቶ ኃይሉ ደጋፊ ሆነው እኛ ደግሞ ሕጋዊን አካሄድ በመከተል የቅንጀትን ዓላማ ተግባራዊ አደርጋለሁ የሚለውን እንደግፋለን ብለን በመሄዳችን "አቶ ኃይሉ የቅንጅትን ስምና ምልክት ይዘን እንድንቀጥል ወክለውን እያለ እናንተ ያለ አግባብ ተጠቅማችሁበት" በሚል ክስ መስርተው ፍርድ ቤት በመሟገት ላይ እንገኛለን። በዚህ ምክንያት ደግሞ ከሁለታችንም ለፈረንጅ ጠበቃ ከ25 ሺህ ዶላር በላይ ወጪ እያወጣን እንገኛለን። ይህ ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ ቢላክ ጥሩ ሥራ ይሠራ ነበር።" ሲሉ አቶ የሱፍ ተናግረዋል።

ከ23 ዓመት በላይ በካናዳ መኖራቸውን የገለፁት አቶ የሱፍ "እኛ በአገራችን ሰብዓዊ መብት እንዲከበር፣ ነፃ ምርጫ፣ ተጠያቂነት እንዲኖር ዜጎች በሠላም እንዲኖሩ ከድህነት እና ከረሃብ እንዲላቀቁ ነው የምንፈልገው። ለዚህ ደግሞ በጋራ ተባብረን፣ ተጋግዘንና ተስማምተን መሥራት ሲገባን፤ ከህዝብ ጥቅም ይልቅ የግል ጥቅም የሚያስቀድሙ ፖለቲከኞች ትግሉን እያበላሹት ነው።" ብለዋል።

ገንዘቡን በሚመለከት ቻፐተሮቹ የተቋቋሙት በየአገራቸው ሕግ መሠረት በሕግና በደንብ እንዳለ አቶ ኃይሉ ወይም ለብርትኳን አሊያም ለዶ/ር ብርሃኑ ገንዘብ ለማሰባሰብ እንዳልሆነ ተናግረዋል።

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ከሚያገኘው ላይ እየቆጠበ የሚያዋጣው ለሀገሬ የሚጠቅም ነገር ከሆነ ብሎ እንጂ ግለሰቦች እንደፈለጋቸው እንዲያባክኑት ወይም በፈለጉ ጊዜ አንጡ፣ ወይም እንከሳለን እያሉ አስፈራርተው እንዲወስዱ አለመሆኑን ጠቁመዋል።

አቶ ዮሱፍ ዑመር አያይዘው እንደገለፁት፤ "ቻፕተሮቹ የተቋቋሙት ኢትዮጵያ ውስጥ በሕጋዊ መንገድና በሠላማዊ ትግል ዲሞክራሲን ለማስፈን ለሚታገለው ቅንጅት እንደነበር ገልፀው መሪዎቹ በታሰሩ ግዜ ይህ ስም ለሌላ በመሠጠቱ፤ የቅንጅቱን ዓላማና መርህ ተከትለው ሕጉንና ደንቡን አክብረው እየተንቀሳቀሱ ለሚገኙት ለአንድነት ፓርቲ ድጋፋችንን እየሰጠን ነው። ከዚህ ውጪ ማንም ሊጠይቀን የሚችል የለም። እንዲጠይቀን የሚያስገድድም ሆነ የሚፈቅድ የሕግ አግባብ የለም።" ብለውናል።

## አውሮፓ

ይህንኑ በማስመልከት በአውሮፓ ካሉት ስዊድን፣ ለንደን፣ ኖርዌይ፣ ስዊዘርላንድና አውስትራሊያ አምስት ቻርተሮች የስዊድኑን ሊቀመንበር አቶ ታምራት አዳሙ አነጋግረናቸው ነበር። አቶ ታምራት ስለጉዳዩ ሲያብራሩ፤ የድጋፍ ማኅበሮቹ ራሳቸውን የቻሉ እንደሆኑና መሪዎቹ በእስር በነበሩበት ወቅት እነሱን ለማስፈታት በጋራ መሥራታቸውን ገልፀው፤ አሁን ደግሞ ሁሉም ተለያይቶ የየራሱ ፖርቲ እያቋቋመ እንደሚገኝ ጠቁመዋል። እሳቸው የሚመሩት ቻፕተር ኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረገውን ሠላማዊ ትግልና የቅንጅቱን ዓላማ ይዞ በትክክለኛ መንገድ እየተንቀሳቀሰ ያለውን አንድነት ፓርቲ እንደሚደግፍ ገልፀው፤ ከዚህ ውጭ በግለሰብ ስም የተሰበሰበ ገንዘብም እንደሌለና ሊጠየቁ የሚችሉበት አንዳችም የሕግ አግባብ አለመኖሩን አስረድተዋል።

ይልቁንም ቀደም ሲልም የተለያዩ በመሆናቸው በራሳቸው መንገድ ድጋፋቸውን እያሰባሰቡ መሥራት እንዳለባቸው የጠቆሙት አቶ ታምራት፤ "ቻፕተሮቹ ሙሉ ሕጋዊውና ትክክለኛውን አቅጣጫ የያዘውን አንድነት ፓርቲን መደገፍ ሲጀምር ወደ ክስ እንሄዳለን ማለታቸውን ከተራ ንግግር የሚያልፍ ነገር አይደለም። የሕግ አግባብም የላቸውም።" ሲሉ ተናግረዋል።